ልጆቻችሁን ሰባት አመት ሲሆኑ በሶላት እዘዟቸው፤ አስር አመት ሲሞላቸው ሶላት ላለመስገዳቸው ምቷቸው፤ በመካከላቸውም የመኝታ ስፍራቸውን ለዩ!

ዐምር ቢን ሹዐይብ ከአባቱ፣ አባቱም ከአያቱ እንዳስተላለፈው እንዲህ አለ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው
ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "ልጆቻችሁን ሰባት አመት ሲሆኑ በሶላት እዘዟቸው፤ አስር አመት ሲሞላቸው ሶላት ላለመስገዳቸው
ምቷቸው፤ በመካከላቸውም የመኝታ ስፍራቸውን ለዩ!" [ሐሰን ነው።] [አቡዳውድ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አባት ወንድና ሴት ልጆቹን ገና ሰባት ዓመት እያሉ ሶላት እንዲሰግዱ ማዘዝና ሶላትን በማስተካከል ላይ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ማስተማር እንዳለበት ገለፁ። አስር ዓመት የደረሱ ጊዜም ትእዛዙን ይጨምራል። ሶላትን በማጓደላቸው ይመታቸዋልም በመኝታ ስፍራም በመካከላቸው ይለያያቸዋል።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5272